# አይ ሆድ ወንጀለኛ*




እስር የለህ ማፈኛ፣
ልጥጥ እንደ ፊኛ፣
ሌሊት አታስተኛ፣
ቀንም ቀበጠኛ፣
ስትጮህ ሞገደኛ፣
አመልህ ቀበኛ፣
ቀጪ የለህ ዳኛ፣
አይ ሆድ ወንጀለኛ!

ራስን ታስፎክት፣
አንገትን ታስቀትት፣
አይንንም ታስፈጥጥ፣
ማተብን ታስቆርጥ።

አይ ሆድ አዋራጁ፣
ሁሌ እንደጎመጁ፣
በልተው አያፈጁ፣
ኖረው አያረጁ፣
ብለህ ታስጠራቸው
ሁል ጊዜ ያ ልጁ፣
ለትልተው ቢጃጁ!

እንደውሻ አስነካሸ፣
እንደ ጅብ አስቦዳሸ፣
እንደ ድመት አስላሸ፣
አንደ አሳማ አሳፋሸ፣
ስንቱን አንበረከክ
ሆድ የሚሉህ አሳች!

አይ ከርስ ሞልቃቄ፣
ለጭራ አያስበቄ፣
ቆብን አስወልቄ፣
ቀበቶ አስፈልቅቄ።

እንደ አህያ ጫኙ፣
እንደ በሬ አፋኙ፣
እንደ ሙቅ አቅጣኙ፣
እንደ ሙት ከፋኙ፣
አይ ሆድ ብላሽ ከንቱ!

አይ ሆድ መተተኛ፣
ከእግር ሥር ታስተኛ፣
ታሳጥብ ክርነኛ፣
ታስም ጉልበተኛ።

ወስፋት ሰለክላካ!
እንደ ሊጥ ታስቦካ፣
ታዝቅ እንደ አሙካ፣
እንደ አተር ታስከካ፣
ታስርድ እንደ ቡርካ!

ጆሮን ያንሰራራህ፣
አይንን ያቅነዘነዝህ፣
ምላስን ያስተባህ፣
አፍንጫን ያሰፋህ፣
ህሊናንም ያሳትህ፤
አይ ሆድ ወንጀለኛ
ተነግሮ አያልቅ ግፍህ፣
ማነው የሚዳኝህ?
ማን ይሆን አለቃህ?

አለምን ወጥረህ፣
በካስማ ሰቅዘህ፣
በጭንቅ እያጣበብህ፣
እያመስካት ያለህ፤
አቅሙን ማን ዳረገህ?
ስልጣኑን ማን ሰጠህ?

መልክህ እስስተኛ፣
ወርድህ ዝተተኛ፣
አመልህ ቀበኛ፣
ስትወስድ ቀማኛ፣
ውሎህ አውልግኛ፣
ልክፍት እንደ ጋኛ፣
ለጓሚ ህሊና
ቀጭ የለህ ዳኛ፣
አይ ሆድ ወንጀለኛ!!!
አይ ሆድ ወንጀለኛ!!
አይ ሆድ ወንጀለኛ!

በላይነህ አባተ
*ቁዘማ ከሚለው መጽሐፍ በማሻሻል የተወሰደ
ተጻፈ ታህሳስ ፲፱፻፺ ዓ.ም.